# የኤች አይ ቪ/ኤድስ የስርጭት ሁኔታ እና

# የተሰጡ ምላሾች

# ይዘት

- የገለፃው ዓላማ
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ የስርጭት ሁኔታ በባለፉት አስርት አመታት ውስጥ
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ነባራዊ ሁኔታ
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ የስትራቴጂክ እቅዱ ራእይ ግብ ዓላማ እና ስትራቴጂዎች

# የገለፃው ዓላማ



- የኤች አይ ቪ/ኤድስ የስርጭት ሁኔታ መነሻ በማድረግ በስትራቴጂክ እቅዱ በተለዩ ተጋላጭ ተብለው የተለዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ትኩረት በማድረግ የመከላከሉን ስራዎች እና የአገልግሎት ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እና ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ

# ባለፉት 10 ዓመታት የኤች አይ ቪ ስርጭት ሁኔታ

# አዲስ በኤች አይ ቪ የመያዝ ሁኔታ (ከ1990 - 2020)




Hirut A.

# አዲስ በኤች አይ ቪ የመያዝ ሁኔታ

- በ1990 የነበረውን አዲስ በቫይረስ የመያዝ ምጣኔን ከ2020 የመያዝ ምጣኔ ጋር ስናነፃፅረው በ90% መቀነስ ተችሎአል
- ነገር ግን በ2010 የነበረውን አዲስ በቫይረስ የመያዝ ምጣኔን ከ2020 ጋር ስናነፃፅረው ቅናሹ 52% ይሆናል
- ይህም የ2010ን አዲስ የመያዝ ምጣኔ መነሻ አድርጎ በ2020 በ75% ለመቀነስ በዩኤን ኤድስ የተቀመጠውን ታርጌት ማሳካት አልቻለም

# ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማት ባለፉት ዓመታት




Hiut A.

# የቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ

- ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል
- በተለይም ደግሞ Option B+ ከተጀመረበት ከ2013 ዓ.ም ወዲህ የቅናሽ ምጣኔው ከፍተኛ ነበር
- በ2010 የነበረውን ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱ መተላለፍን በ2019 ላይ በ44% መቀነስ ተችሏል

# በኤድስ የሚከሰት የሞት ምጣኔ ከ1990-2020





# የሚሰጡ ጤና ተቋማት ሽፋን በክልሎች በ2020



# የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና

- በ2001 ዓ.ም ከ100,000 ሰው 117.7 ይከሰት የነበረው የሞት ምጣኔ በ2019 ወደ 11.73 ሰው ከ100,000 ሰው ዝቅ ማድረግ ተችሏል
- የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና ከተጀመረበት ከ2005 ጀምሮ የሞት ምጣኔን ነከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል

ለምሳሌ በ2010 የነበረውን የሞት ምጣኔን ከ2019 ጋር ስናነፃፅረው በ52% ቀንሷል

## ➢የኤች አይ ቪ/ኤድስ ነባራዊ ሁኔታ

- የአዋቂዎች የቫይረሱ ስርጭት ምጣኔ - 0.86%
- **622,236** ቫይረሱ በደማቸው ይገኛል

ሴቶች: 383,780 (62%)

ወንዶች: 238,547 (38%)

ህፃናት (0-14): 44,138 (7%)

# ሀገራዊ የኤች አይ ቪ ስርጭት ሁኔታ - 2020

**11,715 አዲስ በቫይረሱ የተያዙ በ2020**

- ወንድ: 4,278 (37%)
- ሴት: 7,437 (63%)
- ህፃናት (0-14): 2,794 (24%)

**12,685 በኤድስ የሞቱ በ2020**

- ሴት: 5,506 (43%)
- ሴት: 7,179 (57%)
- ህፃናት (0-14): 1,96 (16%)

# የኤች አይ ቪ የመጋለጥ ሁኔታ በ2021 ግምት (EPHI 2022)

- የኤች አይ ቪ ተጋላጭነት ከ 19-34 የእድሜ ክልል ከፍተኛ ሲሆን፤ በይበልጥ **ታዳጊ ወጣት ሴቶች** ከ 20-24 የእድሜ ክልል ላይ በጣም ከፍተኛ ነው




Hirut A.

# የኤች አይ ቪ የመጋለጥ ሁኔታ በ2021 ግምት (EPHI &FHAPCO 2021)

- የኤች አይ ቪ ተጋላጭነት በሴተኛ አዳሪዎች ደንበኞቻቸውን ከሚያገኙባቸው ቦታዎች



# የኤች አይ ቪ የመጋለጥ ሁኔታ (EHIA 2018, EPHI 2022)

**የኤች አይ ቪ ተጋላጭነት ባሎቻቸውን የፈቱ እና የሞተባቸው ሴቶች**



<

# የ5 ዓመቱ የስትራቴጂክ እቅዱ ራእይ ግብ አላማዎች እና ስትራቴጂዎች

- ራዕይ፡-
  - ከኤድስ ነጻ የሆነች ኢትዮጵያ ማየት

- ተልዕኮ፡-
  - የላቀ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልናመቆጣጠር ፕሮግራሞችን **ተቋማዊ በሆነ** መልኩ እንዲተገበሩ በማድረግ፣ አገር አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽን **በማስተባበር፣ የጤና ሥርዓትንና የፕሮግራምና ማህበራዊ አስቻይ ሁኔታዎችን በማጠናከር** በቀጣዮቹ ዓመታት የኤች አይ ቪ ስርጭት ቁጥጥር ግብን ማሳካት፣

# ስትራቴጂክ ዓላማዎች



**ዓላማ 1፡-**

- እ.ኤ.አ በ2025 90% የሚሆኑትን ለኤችአይቪ **ይበልጥ ተጋላጭ** የሆኑ እና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን በጥምር የኤችአይቪ **መከላከል** አገልግሎቶች ተደራሽ ማድረግ፣

- **ዓላማ 2፡-**
  - ኤችአይቪ ምርመራ አገልግሎትን በማጠናከር እኤአ በ2025 **95%** የሚሆኑት ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎች ተመርምረው **ውጤታቸውን እንዲያውቁና** አስፈላጊውን ህክምናና መድሃኒት እንዲያገኙ ማድረግ፣

# የቀጠለ...



- **ዓላማ 3፡-**
  - እ.ኤ.አ በ2025 የኤችአይቪ እና ቂጥኝን ከእናት ወደ ልጅ መተላለፋቸውን መግታት፣
- **ዓላማ 4፡-**
  - እ.ኤ.አ በ2025 95% የሚሆኑት ኤችአይቪ በደማቸው እንደሚገኝ ያወቁ ሰዎች የጸረ-ኤችአይቪ መድሃኒት እንዲወስዱና መድሃኒቱን ከሚወስዱት ውስጥም **95%** የሚሆኑት በደማቸው ያለው የቫይረስ ልኬት መጠን በሚፈለገው ደረጃ እንዲወርድ ማድረግ፣

# የቀጠለ…

- **ዓላማ 5፡-**
  - ለዘርፈብዙ ምላሹ ማስፈጸሚያ የሚሆን **ሃብት ማሰባሰብና** የተገኘውን ሃብት የላቀ ውጤታማነት በሚያመጣ መልኩ መደልደልና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

- **ዓላማ 6፡-**
  - መረጃ ላይ የተመረኮዘ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ **ስትራቴጂክ መረጃዎችን ማመንጨትና** ጥቅም ላይ የማዋል አሰራርን ማጠናከር፣

# የማህበረሰብ ክፍልን መሠረት በማድረግ ቅድሚያ መስጠት



- ሴተኛ አዳሪዎች
- የሕግ ታራሚዎች
- አደንዛዥ ዕፅ በመርፌ የሚወስዱ/የሚወጉ ሰዎች(መከላከል )
- ለኤችአይቪ ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው አዳጊና ወጣት ሴቶች
- የትዳር አጋራቸውን የፈቱ/የሞተባቸውን ሴቶችና ወንዶች
- የቀን/ተንቀሳቃሽ ሠራተኞች
- የረጅም ርቀት አሽከርካሪዎች
- ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖችና ቤተሰቦቻቸው

# መልክዓ ምድር መሠረት በማድረግ ቅድሚያ መስጠት



- ✓ ከፍተኛ ስርጭት ያላቸው ወረዳዎች፡- በሀገራችን 265 ሲሆኑ እንደ አዲስ አበባ **48** ሲሆኑ አዲስ የመያዝ ምጣኔ ***≥0.03%*** የሆነባቸው ናቸው፡፡
- ✓ መካከለኛ ስርጭት ያላቸው **(Medium incidence)** ወረዳዎች፤ **326** ወረዳዎች ሲሆኑ አዲስ የመያዝ ምጣኔ **0.01% - 0.029%** የሆነባቸውና መካከለኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው
- ✓ ዝቅተኛ ስርጭት ያላቸው **(Low incidence)** ወረዳዎች፤ **485** ወረዳዎች ሲሆኑ አዲስ የመያዝ ምጣኔ ከ ***0.01%*** በታች የሆነባቸው ናቸው

# መልክዓ ምድር መሠረት በማድረግ ቅድሚያ መስጠት



- ከተሜነትና የትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች መበራከት በከተሞች ያለውን የቫይረሱን የስርጭት ሁኔታ ከፍ አድርጎታል
  - አምራች የሰው ሀይል ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ እድል መፍጠሩ
  - ቫይረሱ እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችና ቦታዎች መስፋፋታቸው
- አዲስ አበባ ያለው ከፍተኛ ጫና የዚህ ማሳያ ነው

**በ11 ክፍለ ከተማ የሚገኙ ለኤች አይ ቪ ስርጭት ምቹ የሆኑ አካባቢዎችን (Hot spot areas) ተለይተዋል።**

- ቡና ቤቶች (*Bars*)
- ግሮሰሪዎች (*Groceries*)
- ፔንሲዮኖች (*Pensions*)
- የእንግዳ ማረፊያ ቤቶች (*Guest houses*)
- ሆቴሎች (*Hotels*)
- ማሳጅ ቤቶች (*Massage houses*)

## የቀጠለ…



- ሽሻ ቤቶች **(*Shisha houses*)**
- የምሽት ክለቦች **(*Night clubs*)**
- መጠጥ ቤቶች **(*Drinking establishments* )**
- በቱሪስት የሚዘወተሩ መዝናኛ ስፍራዎች **(*Tourist frequented settings*)**

# ሴቶቹ ላይ የቫይረሱን ስርጭት የሚያባብሱ ተግባራት እና ባህሪያት

- ከጠባይ ጋር የተያያዙ **(Behavioural Factors)**
- ከአገልግሎት ጋር የተያያዙ **(Biological Factors)**
- ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት **(Socio-economic Factors)**

# ከጠባይ ጋር የተያያዙ (Behavioural Factors)



- የእውቀት ውስኑነት (መሰረታዊ እውቀትን ብናይ)
  - ሀገራዊ (20% የሴቶች 38% የወንዶች)
  - በአዲስ አበባ በሴቶች 44.1% በወንዶች 51.5%
- ጥንቃቄ የጎደለው ወሲባዊ ግንኙነት በስፋት መኖር
- ቀጣይነት የሌለው የኮንዶም አጠቃቀም መኖር
- አደንዛዥ እና አደገኛ መድሀኒቶች የመጠቀም ተግባራት
- እንደ አስገድዶ መድፈር ያሉ ፆታዊ ጥቃቶች

# የቀጠለ...



- ወሲብን መጀምር ከሚገባው እድሜ አስቀድሞ መጀመር
- የወጣት ልጃገረዶች ወሲብን ለገቢ ማግኛ የመጠቀም ሁኔታ
- ድንግልናን መሸጥ
- ለትዳር ታማኝ አለመሆን
- የወሲብ ጓደኛን መቀያየር
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የተሳሳቱ እምነቶች እና አመለካከቶች አሁንም ድረስ መኖር

# ከአገልግሎት ጋር የተያያዙ (Biological Factors)

- ህገ ወጥ የውርጃ ተግባራት
- የተለያየ የምርመራ ውጤት ያላቸው ተጣማሪዎች (Discordant couples) መኖር
- አሁንም ድረስ ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፍበት ሁኔታ መኖር

# ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት (Socio-economic Factors)

- እንደ ጫት ቤቶች፣ ሺሻ ቤቶች፣ አረቄ ቤቶች፣ የምሽት ክለቦች፣ ግሮሰሪዎች፣ ቡና ቤቶች፣ ሆቴሎች፣ ፔኒሲዮኖች፣ የእንግዳ ማረፊያ ቤቶች ወዘተ በስፋት መኖር
- የቤተኛ አዳሪዎች በብዛት መኖር እና ወሲብን ለገቢ ማግኛ የመጠቀም ሁኔታ በስፋት መቀጠል
- ከፍተኛ የሆነ የህዝብ እንቅስቃሴ መኖር

# የተቀናጀ ፕሮግራም እና አገልግሎት



| ባህሪያዊ / Behavioral/ | መዋቅራዊ /structural / | የኤችአይቪ ጤና አገልግሎት/Biomedica |
|---|---|---|
| • የአቻለአቻ ትምህርት | • አሳታፊ ፕሮግራም | • የኮንዶም አቅርቦት |
| • የእህቶች ለእህቶች ፕሮግራም | • ድጋፍ ሰጪ ቡድን | • የኤችአይቪ ምክክርና ምርመራ |
| | • ሪፈራል ሊንኬጅ | |
| • የህይወት ክህሎት | • የማህበረሰብ ንቅናቄ | • የአባላዘር በሽታ ህክምና |
| • የምክክር አገልግሎት | • አድቮኬሲ | • የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት |
| • የኮንዶም ትዉዉቅ | • ፓርትነር ሽፕ | |
| • የአዉትሪች ፕሮግራም | | • የፀረ-ኤችአይቪ መድሀኒት |

# ባህሪያዊ / Behavioral/



- ✓ አመቺ በሆኑ መንገዶች ወቅታዊ መረጃዎችን ማቀበል
- ✓ ግንዛቤዎችን ማስጨበጥና የተሟላ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ
- ✓ ከበሽታ መከላከል የሚያስችል ክህሎት እና አመለካከት እንዲኖራቸው ማስቻል

# የህይወት ክህሎት ትምርት



# አገልግሎት Biomedical



- ኮንዶምን በአግባቡ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተጠቃሚ መሆን **(ኮንዶም የሚጠቀሙት 65 ከመቶ አይበልጡም)**

- ከኤች አይ ቪና አባላዘር በሽታዎች እራሳቸውን እንዲጠብቁ መመርመር

- ቅድመ ኤች አይ ቪ የመከላከል መድኃኒት አገልግሎት (Prep)

# አገልግሎት Biomedical





# መዋቅራዊ/structural

- ✓ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ውይይት ማድረግ
- ✓ የጤና ስርዓትን ማጠናከር
- ✓ የማረፊያ እና የመማማሪያ ማእከላት አገልግሎት
- ✓ የገቢ ማስገኛ ስልጠና እና የመነሻ ካፒታል ድጋፍ


[redacted]
[redacted]

# የማህበረሰብ ተሳትፎን ማረጋገጥ





# ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰብ ቁጥር



| | በ 2020 | **በ 2025** |
|---|---|---|
| ሴተኛ አዳሪዎች | 210,000 | 240,000 |
| የትዳር ጓደኛቸውን የፈቱ/የሞተባቸው ሴቶችና ወንዶች | 956,475 | 1,114,931 |
| ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉና ለኤችአይቪ ከፍተኛ ተጋላጭና ትያላቸው አዳጊና ወጣት ሴቶች | 134,341 | 147,426 |

# የ 2014 ዓ.ም የተጋላጭ ሴቶች አፈፃፀም



| **መለኪያዎች** | ነባራዊ መነሻ | **2014 ኢላማ** | የዓመቱ አፈፃፀም | **አፈፃፀም በ %** |
|---|---|---|---|---|
| በጥልቅ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት የተደረሱ ሴተኛ አዳሪዎች ብዛት | 16,011 | 20,081 | 19,714 | 98% |
| በጥልቅ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት የተደረሱ የትዳር ጓደኛቸውን የፈቱ/የሞተባቸው ሴቶችና ወንዶች ብዛት | 51,080 | 95,946 | 11,665 | 12% |
| በጥልቅ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ተደረሱ ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉና ለኤችአይቪ ከፍተኛ ተጋላጭና ትያላቸው አዳጊና ወጣት ሴቶች ብዛት | 3,134 | 1,776 | 7,147 | >100 % |

# የ 2014 ዓ.ም የተጋላጭ ሴቶች አፈፃፀም

| **መለኪያዎች** | **ነባራዊ መነሻ** | **2014 ኢላማ** | **የዓመቱ አፈፃፀም** | **አፈፃፀም በ %** |
|---|---|---|---|---|
| የኮንዶም ስርጭት | | | | |
| የተለየ ትኩረት ለሚሰጣቸውና ለአጠቃላይ ማህበረሰብ | | 1,286,883 | 6,654,153 | >100% |
| ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ እና ሌሎች ትኩረት ለሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች | | 28,385,488 | 9,712,039 | 34% |

# የማህበራዊና የፕሮግራም አስቻይ ሁኔታዎች

# ሥርዓተ ጾታና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን መከላከል

**በጤናው ሴክተር:-**

- ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከልና በተሟላ መልኩ ምላሽ ለመስጠት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን ፣
- በጤና ሴክተር ያሉ ሴቶችን አቅም ማጎልበት (በውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች በመመደብ ጭምር)፣
- ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸውን ሰዎች የተሟላ የጤና አገልግሎት ምርመራ፣ ኤችአይቪ ምርመራ፣ የአባለዘር በሽታዎች ምርመራና ህክምና፣ የእርግዝና ምርመራ፣ ቅድመ-መጋለጥ መከላከያ መድኃኒት፣ ድንገተኛ የወሊድ መከለከያ፣ የጸረ-ኤችአይቪ ህክምና) መስጠት፣ የምክር አገልግሎት፣ ማህበራዊና ህጋዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በሪፌራል ትስስር) መስጠት፣

- **የትምህርት ቤት የልጃገረዶች ክለብ ማጠናከር፣ ወጣት ማዕከላትና የወጣቶች** ክሊኒኮችን ለልጃገረዶች ምቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግና የተቀናጀ አገልግሎት ማለትም የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የኤችአይቪ አገልግሎት፣ የጾታዊና ስነ-ተዋልዶ ጤና እና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣

- ሥርዓተ-ጾታ ፍትሐዊነትና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ምላሽ ዙሪያ **ማህበረሰብ አቀፍ ውይይትን** በማካሄድ የችግሩን ጥልቀት፣ መንስኤውንና መፍትሔዎቹ ላይ የድርጊት መርሐ-ግብር በማዘጋጀት ምላሽ መስጠት፣

- ሥርዓተ ጾታን ያካተተ **የመረጃ ስርዓት** እንዲኖር በማድረግ አፈጻጸሙን መከታተል፣

# ማግለልና አድልዎ

- **የማህበረሰብና የሀይማኖት መሪዎችን** በመጠቀም ስለማግለልና አድልዎ ማስተማር፣ ተማጓችነትና የተግባቦት ሥራ ማከናወን፤
- ማግለልና አድልዎን ለማስቆም ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችና ማህበራትን **አቅም ማጎልበት** ፤
- ስለማግለልና አድልዎ **ሚዲያን** በመጠቀም የተግባቦት ሥራና የተሟጋችነት ሥራ እንዲከናወን ማድረግ ፤
- ስለማግለልና አድልዎ **የጤና ባለሙያዎች ያላቸውን ዝንባሌ ዳሰሳ** ማካሄድ ፤
- **ጸረ- ማግለልና አድልዎ ህጎችና ደንቦች** ተፈጻሚነት ክትትል ማድረግ ፤
- የማግለልና አድልዎ ደረጃ የሚያሳይ ጥናት(**Stigma Index Study**) ማካሄድ ፤
- ማግለልና አድልዎ ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ **የጤና ኤክስቴንሽን** ፕሮግራም ፣ የጤና ልማት ቡድንና የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ **ጥምረት በ**መጠቀም የማህበረሰብ ውይይት ማካሄድ ፤

# የሲቪክ ማህበራት ሚና

- ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችና ማህበራት የፕሮግራም ትግበራን ይደግፋሉ፣ስለተግባራዊነቱ ይሟገታሉ፣ ክትትልም ያደርጋሉ፣
- የሲቪክ ማህበራት ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ እና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ማህበረሰብ ክፍሎችን ይደግፋሉ ፣
- ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ማህበረሰቡ በአጠቃላይ በማግለልና አድልዎ፣ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት፣ የኤችአይቪ አገልግሎት ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እና ለተጎጂና ተጋላጭ አካላት የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት እንዲሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፣
- ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ እና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ማህበረሰብ ክፍሎች በክለብ፣ በቁጠባ ቡድንና በአቻ ቡድን እንዲደራጁ ማብቃትና ድጋፍ መስጠት፣
- የሙያ ማህበራት የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጡ ይደረጋል ፣
- የግል ጤና ተቋማት የኤችአይቪ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣
- አጋርነትን ማጠናከርና የተለያዩ አደረጃጀቶችን (Platforms ) ጥቅም ላይ ማዋል

# የኤችአይቪ ምላሹን በሰብዓዊ መብት ማቀፍ፣

- የኤችአይቪ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች ሰብዓዊ መብትና የህክምና ስነ-ምግባርን በተከተለ መልክ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማስቻል፣
- የኤችአይቪ አገልግሎት በሚመለከት በሚከሰቱ የፖሊሲና የቁጥጥር መሰናክሎች ዙሪያ ውይይትና ሙግት እንዲካሄድ ማድረግ ፣
- ህግ አውጪዎችና ህግ አስፈጻሚ አካላትን ኤችአይቪ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ ፣
- ተጠቃሚዎች መብታቸውን እንዲያውቁ የህግ ግንዛቤ ማሳደግ ፣
- ከኤችአይቪ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሥርዓተ ጾታ ኢፍትሐዊነት ፣ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መቀነስ ፣
- የማህበረሰብ ንቅናቄና ተሟጋችነትን ማጠናከር ፣

# የጤና ስርዓትን ማጠናከር፣

- የግብዓት አቅርቦት ሰንሰለትን ማጠናከር፤
  - የአቅርቦት ትንቢያና ግዥ ሥርዓቱን ማጠናከር፣
  - የግብዓት ስርጭት ሥርዓቱን ማጠናከር ፣
  - የጸረ-ኤችአይቪ ፋርማሲ አገልግሎት ማጠናከር፣
  - የተጓዳኝ በሽታዎች፣ የአባለዘር በሽታዎችና የላቦራቶሪ እና የኪት አቅርቦቶች የፋይናንስ ምንጭ ማጠናከር፣
  - የኮንዶም አቅርቦትና ስርጭት ሥርዓት ማጠናከር፣
  - በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ማጠናከር ፣
  - የግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ሥርዓቱን ማሻሻል ፣
  - የግል ተቋማት በአቅርቦት ሰንሰለት ያላቸውን ሚና ለማሳደግ የሚያስችል የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ ፣

# አስተዳደር፣አመራር፣ ማስተባበርና ተጠያቂነት፣

- በየደረጃው ተጠያቂነትን ማስፈን በሚቻልበት መልክ ብሔራዊ የኤድስ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት መከለስ፣
- **የክልል የኤድስ ምክር ቤቶች** በክልል ደረጃ ተጠያቂነትን ማስፈን እንዲቻል በማድረግ እንደገና ማደራጀት፣
- የፌዴራልና የክልል ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ **ጽ/ቤቶች አደረጃጀት** ፣ **ኃላፊነትና ተግባር** ለአሁናዊ በሽታ ሁኔታ ምላሽ **በሚሰጥበት መልክ መከለስ** ፣
- የፌዴራል ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤትን ስትራቴጂክ ዕቅዱን ለመተግበርና ቀጣይነት ያለው የኤችአይቪ ስርጭት ቁጥጥር ዕውን ለማድረግ **በሚያስችል መልኩ በሰው ኃይል ማጠናከር** ፣

# አጋርነት፣ ዘርፈ–ብዙ ትብብር፣ ሲቪክ ማህበራትና የግል ሴክተር ተሳትፎ፣

- **ዘርፈ–ብዙ ትብብር፣**
  - **ስትራቴጂክ ሴክተሮችን ቅድሚያ** በመስጠት በኤችአይቪ ምለሹ ትርጉም ባለው መልክ ተግባራዊ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን የሚከተሉት ተግባራት ታቅደዋል ፡፡
  - ✓ የሴክተሩ አመራር ባለቤትነትን ማረጋገጥ በሚቻል መልክ **ሜይንስትሪሚንግን ትግበራን** ማሻሻል ፣
  - ✓ ለኤችአይቪ ምላሹ **ቁልፍ የሆኑ ሴክተሮችን አቅም ማጎልብት** ፣
  - ✓ **ቁልፍ ሴክተሮች** ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ እና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማህበረሰብ ክልፍሎችን ተደራሽ በሚያደርግ **መልኩ ማጠናከር** ፣
  - ✓ የኤችአይቪ ጠቋሚዎችን በቁልፍ ሴክተሮች **የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ጋር** ማቀናጀት ፣

# ፖሊሲ

- የኤድስ ፖሊሲውን ወቅቱ በሚፈልገው መልኩ መከለስ ፣
- ፖሊሲ ትንተና በማካሄድ ለኤችአይቪ አገልግሎት እንቅፋት የሚሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮችን ማሻሻል ፣

- ተጋላጭ ተብለው የተለዩ ሴቶችን እንዴት እንለያቸው?
- በባህሪ ለውጥ ስራዎቹ እንዴት እንደርሳቸዋለን?
- የአገልግሎት ተጠቃሚነታቸውን እንዴት እንጨምር?

ከእኛ ምን

ይጠበቃል???

# Great Thanks